# ዴሞክራሲ በሂደት …

ታደገ ከካዛንቺስ 07/14/09

የዜጐች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የተከበሩባትና መልካም አስተዳደር የነገሰባት ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለማየት መላው ሕዝባችን ተመኝቷል፣ ታግሏል፣ ብዙዎችም ለዚሁ አላማ መስዋዕት ሆነዋል፡፡ ዴሞክራሲያዊ ስርዓትን የመገንባት አላማ የትውልዶች ምኞት፣ ህልምና የትግል አላማ ሆኖ ቆይቷል፡፡

ዜጐች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብታቸው የሚከበርበት ሁኔታ እንዲፈጠር መመኘታቸውም ሆነ ለዚህ ለተቀደሰ አላማ መታገላቸው የሚገርም አይደለም፡፡

ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደርን ማስፈንና የሕዝብን መብትና ጥቅም ለማስከበር የግድ መሟላት ያለበት ራሡን የቻለ ትልቅ አላማ ነበርና፡፡ ነገር ግን ዴሞክራሲ በአገራችን ተፈላጊና አማራጭ የሌለው የሚሆነው ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር ራሣቸው ጠቃሚና ተፈላጊ ነገሮች ስለሆኑ ብቻ ሳይሆን በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ የህልውና ጉዳይ ስለሆነም ጭምር ነው፡፡

አገራችን ለረጅም ጊዜ በፀረ ዴሞክራሲያዊ አገዛዝ የማቀቀችና ዜጐችም መብታቸውንና ጥቅማቸውን በህጋዊና በሠላማዊ መንገድ ማስጠበቅ የሚችሉበት ዕድል የተነፈጉባት አገር ነበረች፡፡ የጭቆናው ቀንበር በላይ በላዩ እየተከማመረ ሲመጣና ተሸክመውት መቆየት የማይችሉበት ደረጃ ላይ በመድረሳቸው አምባገነኑን የደርግ አገዛዝን ለመጣል ቆርጠው በመነሳት በተባበረ ክንድ ከሥልጣን ሊያስወግዱት ችለዋል፡፡

የደርግ ስርዓት ከወደቀበትና ኢህአዴግ አገሪቱን ከተረከበበት ከግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ/ም ማግስት ጀምሮ አገሪቱን ከገባችበት አዘቅት ለማውጣት በርካታ ጥረቶች ተደርገዋል፡፡ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በመፈቃቀድና በመቻቻል ላይ ለተመሠረተው ዴሞክራሲያዊ አንድነት ፅኑ መሠረት ለመጣል በቅተዋል፡፡ ከ15 እና 16 ዓመታት ባልበለጠ ጊዜም የኢትዩጵያ የዴሞክራሲ የጉዞ

ሂደት በፈጣን ሁኔታ እያደገ መምጣቱንና የዴሞክራሲ በሂደት ማደግን ያስመሠከረ ሊሆን ችሏል፡፡

በተገኘው የዴሞክራሲያዊ ሂደት የተለያዩ የፓለቲካ ፓርቲዎች ተፈጥረው በዴሞክራሲያዊ መንገድ ሕዝቡ የሚመስለውን እና ይሠራልኛል ያለውን በተለያዩ ጊዜያት በምርጫ ካርዱ መርጧል፡፡ ፓርቲዎችም በዚሁ ጊዜ የአየር ሽፋን አግኝተው የምረጡኝ ዘመቻን አካሂደው በአገሪቱ በታሪካዊ መልኩ የ1997 ዓ/ም አገራዊና ክልልዊ ምርጫ መካሔዱ ይታወሳል፡፡ የ1997 ዓ/ም ምርጫ አስገራሚና በርካታ ሁነቶች የተስተናገዱበት ሆኖ አልፏል፡፡

ይሁንና የ2002 ዓ/ም አገራዊና ክልልዊ ምርጫ በተቃረበበት በዚህ ወቅት የተለያዩ የፓለቲካ ፓርቲዎች ስለምርጫው ዝግጅት ማድረጋቸውን በመዘንጋት ይሁን በጭፍን ጥላቻ የፓለቲካ ምህዳሩ ጠቧል፣ መላወሻ አጥተናል በማለት እንደዘወትር ፀሎት ሲደጋግሙት ይደመጣሉ፡፡ ይባስ ብሎ ደግሞ ስልጣን መያዝ የሚቻለው በምርጫ አሸንፎ ሳይሆን በአቋራጭ በፀረ-ዴሞክራሲያዊ አካሔድ ህገ-መንግስቱን በአመፅ በመናድ ነው በማለት አማራጭ ቀይሰው የተንቀሳቀሱም ማየት ተጀምሯል፡፡

ታዲያ ይህ አይነት የትግል ስልት ያዋጣል ትላላችሁ? በእውኑ ዴሞክራሲያዊ የፓለቲካ ስነ ምህዳሩ ጠቧል? የጠባባቸውስ ለየትኞቹ ይሆን? ጥያቄዎቹን ለመመለስ ጠቢብ መሆን ሳያስፈልግ ካለው ነባራዊ ሁኔታ ተመልክቶ መገንዘብ መቼም የሚያስቸግር አይደለም፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ የፓለቲካ ምህዳር ምን ማለት እንደሆነና ጠበበ የሚባለውስ መቼና ምን ሲሆን እንደሆነ መመልከቱ ጠቃሚ ነው፡፡ ጀርገን ሀበርማስ የተባለ የፓለቲካ ምሁር የፓለቲካ መድረክ ‹‹በአንድ አገር የሚኖሩ ሕዝቦች ተገናኝተው በማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳይ ላይ የጋራ ጥቅማቸውን መሠረት ያደረጉ ጉዳዩችን በነፃነት የሚወያዩበትና በፓለቲካ ጉዳይ ላይ በመሠላቸው መልኩ የራሳቸውን ሃሳብ መስጠት የሚችሉበት ስፍራ ማለት ነው›› በማለት

ሲገልፀው የፓለቲካ መድረክን ማስፋት የሚቻለውም ሕዝቡ በአገሩ ጉዳይ ላይ መንቀሳቀስ ሲችልና ተሳትፎው ሲረጋገጥ መሆኑን ጨምሮ ያስረዳል፡፡

ዴሞክራሲና የፓለቲካዊ ጉዳዩች ከዜጐች መብት ጋር በቀጥታ የተሣሠሩ እንደሆኑና መነሻቸውም ሕገ መንግሥቱ እንደሆነ በገዢው ፓርቲ በኩል በተደጋጋሚ ሲገለፅ ከርሟል፡፡ አንዳንድ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ደግሞ የውጪ አገር ዜጐች በዴሞክራሲው ጉዳይ ላይ ሊሳተፉ ይገባል በማለት ስለዴሞክራሲዊ የፓለቲካ ምህዳሩ መጥበብና መስፋት መነጋገር ከጀመሩም ሰነባብተዋል፡፡ የተወሰኑ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ደግሞ ዴሞክራሲያዊ የፓለቲካ ስነ ምህዳሩ የጠበበበትም ሆነ የሠፋበትም ሁኔታ አለ፣ በጭፍን ጠቧል መባሉን ባለመቀበል ቀድሞውኑ ወደተቃዋሚ ጐራ የተሠለፍነው ዴሞክራሲያዊ የፓለቲካ ስነምህዳሩን አሁን ካለበት ደረጃ ለማስፋትና ሠላማዊ ትግል ለማድረግ ነው በማለት ሲያብራሩ ተደምጠዋል፡፡ ይህንንም የኢትዮጵያ ራዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት ካዘጋጀው የውይይት መድረክ ለመረዳት ችያለሁ፡፡

የኢትዮጵያ ራዲዮና ቴሌቪዥን ይህን መሠል የክርክር መድረክ ማዘጋጀቱ በአገራችን የሚንቀሣቀሱ የፓለቲካ ፓርታዎችን ምንነት እና ያላቸውን አላማ ለሕዝቡ ለማሣየት መጀመሩ እሠየው የሚያስብል ነው፡፡ በዚህ ይቀጥል፡፡ የክርክር መድረክ መከፈቱ በራሱ መንግስት መጪውን ምርጫ ዴሞክራሲያዊ እንዲሆን ለማድረግ ከወዲሁ አቋሙን ያሣየበት ሆኖ ታይቷል፡፡ መድረኩ በራሱ የፓለቲካ ስነ ምህዳሩ እየሰፋ ስለመምጣቱ አንድ ምስክር ሊሆን እንደሚችልና መንግሥት ለዴሞክራሲ ሥርዓት መጠናከር ያለውን ቁርጠኝነት አመላክቷል ማለት ይቻላል፡፡

ለዚህ ውይይት ቅን አመለካከት የሌላቸው መጀመሪያም የሰላም/ሠላማዊ/ ትግልን ያልመረጡ ‹‹ ሥልጣን ባቋራጭ ›› በሚል የተሳሳተ አጀንዳ የሕዝብና የመንግሥት ተቋማትን በማውደም፣ ከፍተኛ የመንግስት ባለሥልጣናትን በመግደል መንበረ ስልጣኑን ለመቆናጠጥ ዘዴ ቀይሰው ብቅ ያሉም አልጠፉም፡፡ ዴሞክራሲ በአቋራጭ ማምጣት ቢቻልማ ‹‹ከዛሬ ጀምሮ በመላው አለም ይሠፍን ዘንድ መልካም ፈቃዳችን ስለሆነ በዴሞክራሲ ህብስተ መና ተንበሻበሹ›› በተባለ ነበር፡፡

ነገር ግን ዴሞክራሲ የሚመጣውና ሊዳብር የሚችለው በሂደት መሆኑን ከእውኑና ከተጨባጩ አለም መገንዘብ ይቻላል፡፡ የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ በአውሮፓና አሜሪካ ምናልባት ከ16ኛውና ከ17ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ እየተገነባ የመጣ ሂደት ነው እንጂ በቅፅበት እምርታዊ ደረጃ ላይ የሚደርስ እንዳልሆነ ሊረዱት ይገባል፡፡

ወደ ዋናው ቁም ነገር ልመለስና በ1997 ዓ/ም በተካሄደው አገራዊና ክልላዊ ምርጫ ከ30 በላይ የሚሆኑ የፓለቲካ ፓርቲዎች ህጋዊ ፈቃድ አግኝተው መሣተፋቸው ይታወሳል፡፡ በአሁኑ ጊዜም ከ89 ያላነሡ የፓለቲካ ፓርቲዎች በምርጫ ቦርድ ተመዝግበው እየተንቀሳቀሱ ይገኛሉ፡፡ ይህም የሚያሳየው ህግና ስርዓቱን ተከትሎ ምርጫውን አሸንፎ አገሪቱን እያስተዳደረ ያለው ፓርቲ ለታቃዋሚዎች በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፓለቲካዊ ጉዳዬች ላይ እንዲወያዩና የራሳቸውን ፓሊሲና ስትራተጅ እንዲያስተዋውቁ መድረክ እያመቻቸላቸው መሆኑን ነው፡፡

ፓርላማ ውስጥ ስንመለከት ተቃዋሚ ፓርታዎች የሚሣተፁበት ጠቅላይ ሚኒስትሩን ጨምሮ ከፍተኛ ባለስልጣናት በተገኙበት ያላቸውን ጥያቄና ሃሣባቸውን የሚያቀርቡበት ‹‹የተቃዋሚዎች ቀን›› እና ጠቅላይ ሚኒስትሩ ምላሽ የሚሠጡት ሰዓት መመቻቸቱና ስርጭቱ በቀጥታ በቴሌቪዥን መተላለፁ በዴሞክራሲያዊ ስርዓቱ መጐልበት አስተዋፅኦ ከማበርከቱም በላይ ሕብረተሰቡ የትኞቹ ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ አስተዋፅኦ አላቸው የትኞቹስ የላቸውም? የሚለውን ለመለየትና ያላቸውን አላማ እንዲረዳና ግንዛቤ እንዲጨብጥ ለማድረግ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንደሚኖረው አያጠራጥርም፡፡ ምክንያቱም አንዳንድ ተቀዋሚ ፓርቲዎች በመርህ ደረጃ እንኳ ከየትኛው ቡድን እንደሆኑ ሕብረተሰቡ ለማወቅ የሚቸገርበት ሁኔታ ይታያልና፡፡ አንዳንዶች ደግሞ እውነታውን በመሸፋፈንና ነባራዊ ሁኔታዎችን በመዘንጋት ሊዋጥና ሊላመጥ የማይችል ነገር በማንፀባረቅ በሕዝቡ ዘንድ ትዝብትን እያተረፉ ነውና ምነው አቋማቸውን ቢያስተካክሉ ያሰኛል፡፡

አንዱን ጥሎ አንዱን አንጠልጥሎ ሆነ እንጅ የኔ ነገር ይህን የመሠለ ሰፊ ዕድል ተዘርግቶላቸው በጭፍን አመለካከት የፖለቲካ ምህዳሩ ጠቧል በማለት ተረት ከመለጠጥ ምነው ባለውና በተገኘው በአግባቡ አንድ ቀን እንኳን ቢጠቀሙ፡፡ ታዲያ ማነው ጥፋተኛው? አንዳንዱ እኮ ፓርላማ ውስጥ አመቱን ሙሉ ሳይሳተፍ ጊዜውን የሚገድል የፓርላማ አባል አለ፡፡ ቆምኩለት ለሚሉት የሕብረተሰብ ክፍል የሚሰጡት ምላሽ ሲያጡ የፖለቲካ ምህዳር ስለጠበበ በቂ ተሳትፎ ልናደርግ አልቻልንም በሚል የፌዝ ምላሽ ሊሰጡን ይሞክራሉ፡፡

ሀሳብን በነፃ የመግለፅና የፕሬስ ነፃነትን በተመለከተ አንዳንድ ድርጅቶችና የተቃዋሚ ፓርቲዎች ጭቆና አለ በማለት ሲገልጹ መደመጥም ሌላው ጉዳይ ነው፡፡ እውነት እናውራ ከተባለ እንደ አሁኑ በርካታ የግል የሕትመት ሚዲያዎች እንደአሸን የፈሉበት፤ የተለያዩ ፓርቲዎች እነዚህን ተጠቅመው እንደልባቸው የፈለጉትን ሃሣብ መግለፅና ማንሸራሸር የቻሉበት ዘመን መቼ ታይቶ ይታወቃል? ጥያቄውን ለመመለስ ፈላስፋ መሆን ሳያስፈልግ ህገ መንግስቱን፣ የፓርላማ ህጉን ፣ የምርጫ ቦርድ ህጉን፣ የፕሬስ ህጉንና ተግባራዊ አፈፃፀሙን መመልከት ይበቃል፡፡

ህገ መንግስቱ በአንቀፅ 29 ሃሣብን በነፃ የመግለፅ መብት ሙሉ እውቅና ሠጥቷል፡፡ በሕገ መንግሥቱ መሠረትም ቅድመ ምርመራ ሙሉ በሙሉ ተነሥቷል፡፡ ከፕሬስ ሕጉ ጋር ዜጎች በመንግሥት እጅ ያሉ መረጃዎችን በቀላሉ ማግኘት እንዲችሉ የሚያደርገው የኢንፎርሜሽን ነፃነት ሕግ አብሮ መጽደቁም በኢትዮጵያ ሃሳብን በነፃ የመግለፅ መብት በተግባር እየዋለ ብቻ ሳይሆን በሂደትም እየዳበረ በመሄድ ላይ የመሆኑን ሀቅ መደበቅ " ግመል ሰርቆ ጎንበስ..."ከማለት አይለይም ፡፡

እንደሚታወቀው በኢትዮጵያ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የመድበለ ፓርቲ ሥርዓት የተጀመረበት፣ የሕግ የበላይነትና የሕዝቦች እኩልነት የተረጋገጠበት አሁን ባለው ስርአት ነው፡፡ በፓርቲዎች አማካኝነት ልዩ ልዩ አማራጮችን ለሕዝበ ማቅረብ ሁኔታም የተፈጠረው በዚሁ ጊዜ መሆኑን ማንም ሊክደው የማይችል ሀቅ ነው፡፡

እናም በአሁኑ ጊዜ እየታየ ያለው ችግር ከዴሞክራሲያዊ አድማሱ ሳይሆን ተቋዋሚ ፓርቲዎች በስፋት የተመቻቸላቸውን ሁኔታ በብቃትና በአግባቡ መጠቀም ያለመቻላቸው መሆኑ ሊያስማማን ይችላል፡፡ ምክንያቱም ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓትን አክብሮ በምርጫ አሸንፎ መንግሥታዊ ሥልጣንን ለመረከብ የሚንቀሳቀስ ፓርቲ በምንም መልኩ ፖለቲካዊ አድማሱ ሊጠብበት አይችልም፡፡ ይሁንና የፖለቲካ ፓርቲዎች በሕግ ጥላ ስር ሆነው ሕዝብን ማሳመን፣ ድጋፍ ማግኘትና አማራጭ ማቅረብን እንደአንድ የፖለቲካ ባህል ሊያዳብሩት ይገባል፡፡ ሕጋዊና ሰላማዊ መንገድን ለማይጠቀሙ ደግሞ የፖለቲካ ስነ ምህዳሩ እየጠበበ ይሄድና መዳፈኑም አይቀርም፡፡

ስለዚህ "ሥልጣንን ባቋራጭ" የሚለውን የተሳሳተ አስተሳሰባቸውን በመተው የተጀመረውን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ካለበት ደረጃ እየተሻሻለ እንዲሄድ መደረግ አለበት፡፡ ዴሞክራሲውን ባለው መጠን እንኳ ሳንጠቀምበት የአውሮፓና የአሜሪካን ዴሞክራሲ በመናፈቅ ጊዜያችንን አናጥፋ፡፡ ከምኞት በቀር የምናተርፈው አንዳች ነገር የለምና፡፡ ሠላም!